# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
## የተሰጠ መግለጫ

### ተጠያቂነትን እንጠይቅ

የሕዝብ ድምፅ ሰርቆ የአፈና አገዛዙን በኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ እንደጫነ ለመቀጠል የቆረጠው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ከስመ-ጥፉው ቀይ ሽብር ወዲህ ባልታየ ጭካኔ ሕዝባችንን እያደማና እያስለቀሰ ይገኛል። በጭላንጭል ደረጃ እንኳን በሕግ የሚተዳደር ማንኛውም አገር በእንዲህ ዓይነቱ አለመረጋጋት ወቅት በመንግሥት በኩል ዜጎችን የማሰር እርምጃ ሲወሰድ ጥርት ያለ አሃዝ እየተጠቀሰ ይኸን ያህል ሰው ታሰረ፥ ይኸን ያህል በቁጥጥር ሥር ዋለ፥ ይኸን ያህል ተገደለ፥ ቆሰለ፥ ወዘተ... እየተባለ ተጨባጭ መረጃ ይፋ ይሆናል። በስም፥ በፆታ፥ በዕድሜ፥ ወዘተ... ተለይተው የሚዘረዘሩት ዜጎች በቁጥጥር ሥር የዋሉበት ልዩ ቦታ ለዘመድ ወዳጅ ተገልፆ ታሳሪዎቹ በቤተሰብም ሆነ የእስረኛ ጉዳይን በሚከታተሉ ክፍሎች የመጎብኘት መብታቸው የተጠበቀ ይሆናል። ቤተሰቦችም የታሰሩባቸውን ወገኖች ሄዶ የማየት፥ የመጠየቅና አስፈላጊውን እርዳታ የማቅረብ መብታቸው አይነፈግም።

የሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ ሲነሳ ይኸ የመጨረሻው ዝቅተኛ መሠረታዊ የሕዝብ መብትና እራሱን በመንግሥት ደረጃ ያስቀመጠ ክፍል ሁሉ ግዴታ ነው። በጥበቃ ሥር ያሉ ዜጎች ከዘመድ፥ ከጓደኛ፥ ከሐይማኖት ሰዎች፥ ከሐኪምና ከሕግ አማካሪ ጋር የመገናኘት መብት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 21 እንዲሁም በ1969 ዓ/ም እስረኞችን ለመንከባከብ የወጡ ዝቅተኛ ደንቦች በሚል ስምምነት የተደረሰባቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) የኤኮኖሚና ማኅበረሰብ ምክር ቤት ውሳኔ ቁጥር 207/62 አንቀጽ 44 በቁጥጥር ሥር የዋለ ማንም ዜጋ መታሰሩን ወይም ወደ ሌላ ተቋም መዛወሩን ወዲያውኑ ለቤተሰብ ማሳወቅ የአሳሪው መንግሥት ግዴታ፥ ታሳሪው የዚህ መብት እንዳለው፤ ታሳሪው በቁጥጥር ሥር እንዳለ ሕይወቱ ካለፈ ደግሞ በመንግሥት በኩል ሁኔታውን ለቅርብ የሥጋ ዘመድ የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት በግልፅ ይደነግጋል።
አሁን በአገራችን እንደተከሰተው የዴሞክራሲ ጭላንጭል ጠፍቶ መንግሥትና የጥፋት ኃይሎች ከማንም ቁጥጥር ሥር ወጥተው አንድ ተራ ታጣቂ ወይም አንድ ተራ ካድሬ በዜጎች ላይ የፈላጭ ቆራጭነትና የሞት ሽረት መብት ሲጎናጸፍ ተጠያቂነት የሚባል ነገር ደብዛው ጨርሶ ስለሚጠፋ ይኸ ዓይነቱ ተጠያቂነትና ሃላፊነት የተሞላው ሕጋዊ አሠራር ሊኖር አይችልም። የፋሺታዊ መንግሥት (የፋሽዝም) ምልክቱ ይኸ ነው።

ባለፈው ሰኔ ወር ፺፯ ዓ/ም እና አሁን ደግሞ በጥቅምት ወር ፺፰ ዓ/ም ከመንገድ እየታፈሱ፥ ከሞቀ ቤታቸው በውድቅ ሌሊትም ይሁን በጠራራ ፀሐይ እየተለቀሙና እየታፈኑ ስለተወሰዱት ወጣቶችና ሌሎች ዜጎች ቁጥር በሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት በኩል የተነገረ ነገር የለም። ቤት ይቁጠራቸው ብለን የምንተወው ጉዳይ እንዳይሆን ቤተ-ዘመድ እራሱ ከየቤታቸው ከተለቀሙበት በስተቀር ሌሎች እንደወጡ መቅረታቸውን እንጅ ይታፈሱ፥ ተረሽነው በጅምላ መቃብር ውስጥ ይጣሉ ፥ እንደ ደዴሳ ባሉ በወባ የተበከሉ በረሃማ የማጎሪያ ሰፈሮች ይወርወሩ፥ ከነዚህ ማጎሪያ ሰፈሮች ለማምለጥ ሲሞክሩ የዱር አውሬ እራት ይሁኑ፥ ዓለም-አቀፉ ፀረ-ግርፋትና ስቃይ (ቶርቸር) ድርጅት በኅዳር ሰባት ቀን ባወጣው መግለጫ እንዳሳወቀው አዞ ከበላቸው በርካታ ወጣቶች መኻል ይሁኑ፥

ለአቅመ-ሔዋን ያልደረሱ ልጆቻቸው የመለሰ ዜናዊ ኮማንዶዎች እየተፈራረቁባቸው ለግዴታ ወሲብ ተዳርገው በመሰቃየት፥ በመዋረድና ምናልባትም ለኤድስ በሽታ በመጋለጥ ላይ ይሁኑ አይሁኑ፥ ወዘተ... በማያውቁበት የሰቀቀን ሁኔታ ውስጥ ናቸውና ጉዳዩ በትክክል እንዲጣራ የሚቻለውን ሁሉ የማድረግ ሃላፊነት አለብን፡፡

ስንት ዜጎች በግፍ ተገደሉ? በቶ? አምስት መቶ? ከዚያ በላይ? ፋሽስታዊ አገዛዝ ሲነግሥ ይኸንንም ከወንጀለኛው አገዛዝ ቁንጮዎች በቀር ማንም በውል የሚያውቀው የለም፡፡ የሚታወቀው ቆስሎ ሐኪም ቤት ለመድረስ የበቃው እጅግ አነስተኛ ቁጥር ብቻ ነው፡፡ በየጎዳናው ተደፍቶ ከዚው እሬሳው እየተለቀመ ለጅምላ መቃብር የተዳረገው ስንት ዜጋ ነው? እነዚህ የጅምላ መቃብሮች የት የት ናቸው? ታፍሶ እየተሰቃየም ቢሆን በነፍስ አለልኝ፥ አንድ ቀን ተመልሶ ዓይኑን አየዋለሁ ብላ እናት በተስፋ ከምትጠብቀው ወጣት ስንቱ ነው እንደወጣ የሚቀረው? ዛሬ በሕወሓት/ኢሕአዴግ የግፍ አገዛዝ ሥር ኅብረተሰባችን በባህላችን ቅዱስ የሆነው የዘመድ አዝማድ እርም የማውጣት መብትና ልማድ እንኳን ተነፍጎ እስከ መቸ ነው እንዲህ የምንቀጥለው?

ይኸን ዓይነት ግፍ ዛሬ ተጋግዘንና ታግለን ለማስቆም እኛ እራሳችን ካልተንቀሳቀስን፥ በተናጠል የእያንዳንዱ/እያንዳንዷ ዜጋ በአጠቃላይ ደግሞ የመላው ኅብረተሰባችን ተግባርና ሃላፊነት ነው ብለን ሁላችንም በአንድነት ካልተነሳን፥ በትግሉ የወደቀውን እያነሳን፥ የደማውን እያስታመምን፥ የሚያነባውን እያፅናናን ተያይዘን ወደፊት ለመራመድ ቁርጠኝነትን ማሳያው ጊዜ አሁን ካልሆነ መቸ ነው? ዛሬ ለአገርና ለወገን ጥቅምና ክብር ሲታገሉ የተሰውትንና የተጎዱትን ሁሉ "ቤት ይቁጠራቸው" ብለን ከተውን ነገ የእያንዳንዱን/የእያንዳንዷን ዜጋ ክብርና ኅልውና ክፉኛ ለሚፈታተን እጅግ አስከፊ የአገዛዝ ሥርዓት በሩን እየከፈትን መሆናችንን ሁሉም ጠንቅቆ ሊገነዘበውና የምር ልብ ሊለው ይገባል፡፡

ይኸንን መረን የለቀቀና አቅጣጫ የሳተ የሽብር ድርጊት ዛሬ እኛ ኢትዮጵያውያን ቀርተን ዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡም እየተገነዘበውና እየተቃወመው ለመሆኑ በቅርቡ በተከታታይ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፥ ሂውማን ራይትስ ወች፥ የዓለም-አቀፍ ፀረ-ግርፋትና ስቃይ (ቶርቸር) ድርጅት ያወጧቸው መግለጫዎች ብቻ ሳይሆኑ የአውሮጳ ኅብረት ተወካይ አምባሳደር ቲሞቲ ክላርክ ስለጅምላ መቃብሮችና ሌሎች ግፎች አንስተው "እንዲህ ዓይነት ነገር በኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ታይቶ የማይታወቅ ነው" በማለት ለቢቢሲ ቻናል ፎር ጋዜጠኛ መናገራቸው ተዘግቧል፡፡ የለጋሽ አገሮች አምባሳደሮችም ኅዳር ስድስት ቀን ባወጡት ባለ አሥር ነጥብ መግለጫ መንግሥትም (ኢሕአዴግ) በዚህ በኩል ያለበትን ሃላፊነት ተገንዝቦ አስፈላጊው ሁሉ መረጃ ለቤተሰቦችና ቤተዘመዶች እንዲሰጥ ጠይቀዋል፡፡

የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ከያለበት በዚህ ጉዳይ ወከባ ስላጋጠመው አሥራ-አንድ የሚሆኑ ከዚህ መንግሥት ነፃ ለመሆናቸው ምንም ዋስትና የሌላቸው ግለሰቦች ሰብስቦ "መርማሪ ኮሚሽን" አቋቁሜአለሁ ብሏል፡፡
አንደኛ ነገር ሕወሓት/ኢሕአዴግ "ገለልተኛ" ብሎ ከሚመጻደቅበት የምርጫ ቦርድ ምንም ገለልተኛነት ያልጠበቀውና የማይጠብቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህም ገለልተኛ ተብየ አጣሪ ኮሚሽን ምንም የሚጠብቀው ነገር አይኖረም፡፡
ሁለተኛ ዛሬ ዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብም ተጨምሮበት የኢትዮጵያ ወላጆች ከዚህ አገዛዝ መሪዎች የሚጠይቁት "የታሰሩትን አስረናል፥ የተገደሉትን ገድለናል በሉንና እርማችንን እናውጣ" የሚል ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን እነዚህ የአገዛዙ ቁንጮዎች በያለበት ያጎሩሮቸውንና የረሸኗቸውን ዜጎች ዝርዝር ይፋ ለማድረግ "አጣሪ ኮሚሽን ያስፈልገናል" ሊሉን አይችሉም፡፡ ያውቁታል፡፡

ኅብረታችን በተጠያቂነት መኖር ያምናል፡፡ መኖርም አለበት፡፡ የኢትዮጵያ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች በዚህ መልክ የመጨረሻ ዝቅተኛ የሚባሉ መብቶች አምባሳደሩ

እንዳሉት “ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ” እየተረገጡ ባሉበት ወቅት “ሌላ የድምፅ ማስከበር ትግል አለብን” በማለት የተጠያቂነትን ጉዳይ ችላ ማለት አይችሉም። ታጋይ በገፍ ሲታሰር ባወጣ ያውጣው ሲባል ትግልም መስመር ሊስትና ሊኮላሽ እንደሚችል፥ ታጋይ ሲሞት የትግል መዳከም አደጋ እንዳለ ተገንዝበን ይኸንን ወላጆች ልጆቻቸው የት እንደደረሱ የማወቅና የዘመድ አዝማድን እርም የማውጣት መብት ለማስከበር ቆርጠን መነሳት የትግሉ መቀጠል ብቻ ሳይሆን የኀሊናና የሞራል ጥያቄ አድርገን እንወስደዋለን።

በመሆኑም፤

አንደኛ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች የራሳቸው ሕገ-መንግሥትም ሆነ የተ.መ.ድ. ዓለም-አቀፍ ውሳኔዎች በሚደነግጉት፥ የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ በአንድ ድምፅ በሚጠይቁት መሠረት በቁጥጥር ሥር ስለዋሉም ሆነ በያለበት በህመም፥ በማሰቃየት (በቶርቸር)፥ በጥይት፥ ወዘተ... ሕይዎታቸው ስለተቀጨ ዜጎች መቸ፥ የትና እንዴት ሕይዎታቸው እንዳለፈና የት እንደተቀበሩ፤ በሕይዎት ያሉት የት እንደታሰሩ ለወላጅና ለዘመድ አዝማድ ይፋ እንዲያደርጉ፤ አስፈላጊው መጠለያ፥ ምግብ፥ መጠጥ፥ የሕክምና እርዳታና ሰብዓዊ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው፤

ሁለተኛ በሰኔ ወር ፺፯ ዓ/ም እና በጥቅምት ወር ፺፰ ዓ/ም እንዲሁም ከዚያ ወዲህ እናት፥ አባት፥ ልጅ፥ እህት፥ ወንድም፥ ባል፥ ሚስት፥ ወዳጅ፥ ወዘተ.. የጠፋባቸው ዜጎች ሁሉ የየጠፉባቸውን ወገን ዝርዝር በኢሰመጉ በኩል አስመዝግበው ከአገር ውጭ የሚኖሩ ዜጎች ደግሞ በየአካባቢያቸው በሚገኙ የኢሰመጉ ድጋፍ አካሎች (ኮሚቴዎች) አማካይነት ያላቸውን ሁሉ መረጃ አስተላልፈው አንድ የተማከለ የአቶ መለስ የግፍ አገዛዝ ሰለባዎች ዝርዝር እንዲወጣና ይኸ ተጠናቅሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም ኀብረተሰብ ባስቸኳይ ይፋ እንዲሆን፤

ሦስተኛ ዜጎቻችን ታፍሰው የታሰሩባቸው እስር ቤቶችና ማጎሪያ ቦታዎች ሁሉ ለዓለም-አቀፍ ቀይ መስቀል ማኅበር፥ ለኢሰመጉና ለሌሎች የእስረኞችና የጉዳተኞችን ሁኔታ ለሚከታተሉ ሰብዓዊ ድርጅቶች ክፍት እንዲሆኑና በቀጥታ በጉዳዩ ላይ ክትትልና የሚችሉትን እርዳታ እንዲያደርጉ፥ መንግሥትም በዚህ ረገድ ትብብር እንዲያደርግ አስፈላጊው ሁሉ እንዲደረግ፤ እንደተለመደው ትብብር ካላሳየ ግን ማዕቀብና ልዩ ልዩ አስገዳጅ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የተባበረና የተቀናበረ ዘመቻ ማድረግ፤

አራተኛ በሕወሓት/ኢሕአዴግ ፓርላማ ገለልተኛ ተብሎ የተሰየመው አጣሪ ኮሚሽን በምንም መስፈርት ገለልተኛ ተብሎ የማይታሰብ በመሆኑ በቅርቡ በሊባኖስ እንደተደረገው ሁሉ ገለልተኛና ተአማኒነት ያለው ዓለም-አቀፍ መርማሪ ኮሚሽን ተቋቁሞ ባለፉት ወራት ስለተፈጸሙት ዘግናኝ የመብት ረገጣዎች ምርመራና ማጣራት እንዲደረግና ተጠያቂ የሚሆኑት ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ፤
በአጭሩ ተጠያቂነት እንዲኖር ጠይቀን በተቀናበረ መልክ ባፋጣኝ መንቀሳቀስ ይኖርብናል።

ተጠያቂነትን እንጠይቅ!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ታኅሣስ ፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም